ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ
የድጋፍ ድርጅት በስዊዘርላንድ
KINIJIT SUPPORT ORGANIZATION IN SWITZERLAND
KINIJIT UNTERSTÜTZUNGSORGANIZATION IN DER SCHWEIZ

Postfach 1124, 8152 Opfikon - Switzerland

# የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ድጋፍ ድርጅት በስዊዘርላንድ
# የአቋም መግለጫ

በሀገራችን ለረጅም አመታት ከፍተኛ መስዋዕትነት የተከፈለበትን የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ከዳር ለማድረስ እኛ በስዊዘርላንድ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ከሕዝባችን ጎን በመቆም መከራና ስቃዩን በአካል መጋራት ባንችልም ከቆመለትና ከሚታገልለት ዓላማ ጎን በመሰለፍ ለተከታታይ አመታት በደሉንና ስቃዩን ለአለም ሕብረተሰብ በማሰማት አቅማችን የፈቀደውን ስናደርግ ቆይተናል ።

በተለይም የግንቦት 1997ን ምርጫ ተከትሎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ የተስፋ ራዕይ ይዞ የተነሳውን ቅንጅት በመደገፍ ለድርጅቱ ጥንካሬና ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የበኩላችንን አስተዋጽኦ በማድረግ የዜግነታችንን ግዴታ ስንወጣ የቆየን መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ወደፊትም ፓርቲው በማኒፌስቶው ያስቀመጣቸውን ሀገራዊ ራዕዮች፣ ለሀገራችን አዲስ ተስፋና አማራጭ ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ተግባራዊነት መሰረታዊ መሳሪያ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ከምንግዜውም በላይ በቁርጠኝነት የተነሳን መሆናችንን በድጋሚ ስናረጋግጥ የሚፈጠሩ እንቅፋቶችንም በትዕግስትና በድርጅቱ የስነ ምግባርና መርሆዎች ለመወጣት በመዘጋጀትም ጭምር መሆኑን እናረጋግጣለን ።

ከግንቦት 1997 ምርጫ በኋላ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ሕግና ስርዓትን ባልተከተለ መንገድ በውሰደው እርምጃ  የድርጅቱ መሪዎች ከ 21 ወራት በላይ በእስር ስቃይ ሲንገላቱ በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ፀሐይና የብርድ ቸነፈር ሳያግደን ለመሪዎቻችን መፈታትና ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ስንጮህ ቆይተናል ። ሆኖም መሪዎቻችን በተፈቱ በጥቂት ወራት ውስጥ አብዛኛው አባልና ደጋፊ ባልጠበቀው መልኩ በድርጅቱ መሪ በኩል የታየው ኢ-ዲሞራሲያዊ አካሄድ የድርጅቱን ደንብና ሥርዓት ያልተከተለና ለቅንጅት ራዕይ ሲሉ ደማቸውን ያፈሰሱ፣ አጥንታቸውን የከሰከሱ፣ ለእስራት ለስደትና ለእንግልት የተዳረጉ ወገኖቻችንን ደምና ስቃይ ከምንም ባለመቁጠር የተወሰደ እርምጃ መሆኑን ያመለክታል። ይህም የሚያሳዝን፣ የሚያስተክዝና አንገት የሚያስደፋ ሆኖብናል። በቅንጅት መፈጠር  በአጭር ጊዜ  የነፃነትና እኩልነት መብቴን አገኛለሁ የሚለውን የሕዝብ ተስፋም የሚያደበዝዝና በዚህ አካሄድ ትግሉ ወደ ኋላ እየተጎተተበት እንደሆነም ምሬቱን በይፋ እየገለጸ መሆኑን ነው።

ምንም እንኳ የተከሰተው ኢ-ዲሞክራሲያዊ አካሄድ ብዙዎቻችንን ያስደነገጠና ያስቆጣ ቢሆንም በማንኛውም የፓለቲካ ድርጅት ውስጥ የሚፈጠር ችግርና ሊወገድም የሚችል መሆኑን በማመን በትዕግስት በመጠበቅና የመፍትሄም አካል በመሆን ያደረግነው ጥረት ፍሬ አልባ ስለሆነብን ሀዘናችንን እጅግ የከፋ ያደርገዋል ።

የዲሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባት የተነሳ የፓለቲካ ድርጅት በድርጅታዊ አወቃቀሩም ሆነ አሠራሩ የዲሞክራሲ ጽንሰ ሀሳብን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል። በመሆኑም ቅንጅት የገጠሙትን ውስብስብ ችግሮች በትዕግስትና በዕውቀት ለዲሞራሲያዊ ግንባታ መጠናከር፣የሀገር አንድነትንና ልዑአላዊነትን ለማረጋገጥ ባለው ቁርጠኝነት እንደሚወጣው ምንም ጥርጥር የሌለን ቢሆንም ከድርጅቱ እምነትና ካስቀመጣቸው መርሆዎች ውጭ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች አካሄዳቸውን አንድ ጊዜ ቆም ብለው በማስተዋል የድርጅቱ ሕግና ደንብ ተከብሮ የበለጠ ጥራት ያለው ድርጅታዊ አደረጃጀትና ተግባራዊ ሥራዎችን  እንዲያከናውኑ እናሳስባለን።

መሪዎቻችን ከእስር ከተፈቱ በኋላ የተፈጠሩትና አደባባይ የወጡት አለመግባባቶች በእጅጉ ቢያሳዝነንም የሚመለከታቸው የአመራር አባላት እንደሚያውቁት ሁሉ ችግሩን በውይይት እንዲፈቱ ጥረት አድርገናል። ሆኖም ከሁሉም ወገን ተስፋ ተሰጥቶን ከዛሬ ነገ መልካም እንሰማለን ብለን ስንጠብቅ ያልጠበቅነው እየተከሰተ ችግሩ እየተባባሰ ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ አምርቷል።

በመሆኑም እኛ በስዊዘርላንድ የምንገኝ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት አባላትና ደጋፊዎች በድርጅቱ ውስጥ የተፈጠረውን ሁኔታ በ13/01/2008 በበርን ከተማ የካንቶን ተወካዮች በተገኙበት ባደረግነው ስብሰባ በዝርዝር ተወያይተን የሚከተለው የአቋም መግለጫ እንዲወጣ ወስነናል።

1. ታህሳስ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ለቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የላዕላይ ም/ቤት በሚል በኢንጅነር ኃይሉ ሻውል በተፈረመ ደብዳቤ የአምስት ከፍተኛ አመራር አባላትን ከድርጅቱ ማገድ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 25 / የድርጅቱ ሊቀ መንበር ስልጣንና ተግባር የሚገልጸው / እና የድርጅቱ አመራር አባላት ከድርጅቱ ስለሚታገዱበት ከሚገልጸው አንቀጽ 10/3 ውጭ የተደረገ በመሆኑ እኛም ይህን ድርጅታዊ ማዕከላዊነት ያልተከተለ አሰራርና እርምጃ የምናወግዝ ሲሆን በአስቸኳይ እገዳው እንዲነሳ እንጠይቃለን።

2. በፓርቲው ሕግና ደንብ / 26፣1 / ሊቀመንበሩ በሌሉበት ተቀዳሚ ሊቀ መንበርና እንዲሁም በተዋረድ ሌሎች የአመራር እርከኖች ተክተው መስራር እንደሚችሉ በግልጽ በሕገ ደንቡ ላይ የሰፈረውን በማፍረስ ወይንም በማን አለብኝነት ከላዕላይ ም/ቤቱ እውቅና ውጪ የተሰጠው ውክልና ፍጹም ኢ-ዲሞክራሲያዊ አካሄድ /ድርጊት/ በመሆኑ በአስቸኳይ እንዲነሳ እንጠይቃለን።

3. በድርጅቱ ውስጥ የተፈጠረውን ችግር ለማባባስና ፓርቲውን ለማዳከም ከድርጅቱ ሕግና ደንብ ውጭ በሊቀ መንበሩ የተወሰደውን እርምጃ ተግባራዊ ለማድረግ የሚንቀሳቀሱና ከውስጥም ሆነ ከውጭ ሆነው በቅንጅት ስም እየማሉ በመገዘት ቅንጅቱን የማዳከም ሥራ የሚሰሩ ግለሰቦችንም ሆኑ ቡድኖች ይህን እኩይ ተግባራቸውን እንዲያቆሙ አጥብቀን እንጠይቃለን።

4. የቅንጅት ፓርቲ ሊቀ መንበር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የተፈጠሩትን ችግሮች በድርጅቱ ሕግና ደንብ እንዲሁም ድርጅቱ ለህዝብ ቃል የገባቸውን የስነምግባር እሴቶች ዳግም በማጤን የተፈጠረውን አጣብቂኝ እንዲፈቱ ከተለያዩ ሀገር ወዳድ ወገኖች የቀረበላቸውን ጥሪ ተቀብለው ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት አሁንም እድሉ እንዳለ ተገንዝበው በጽኑ እየተከፋፈለ ያለውን የቅንጅት ቤተሰብ አንድ የሚያደርጉ ጤናማ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ጥሪ እናቀርባለን።

5. የድጋፍ ድርጅታችን አባል የሆነበት የቅንጅት የአውሮፓና አፍሪካ ም/ቤት ታህሳስ 20 ቀን 2007 ዓ.ም ያወጣውን የአቋም መግለጫ የምንደግፍ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ እየገለጽን ም/ቤቱ ችግሮችን ለመፍታት ያደረጋቸውን ጥረቶች እንደምናደንቅ እንዲሁም ም/ቤቱ ወደፊት ቅንጅት አሁን ካጋጠመው ሳንካ ተላቆ ሀገራችንና ህዝባችንን ከግፍና ከመከራ የሚታደግ ሁነኛ የህዝብ እንቅስቃሴ ይሆን ዘንድ ተጨባጭ የድጋፍ ተግባራትን እየወጠነ እንዲራመድ እያሳሰብን ለዚህም የድጋፍ ድርጅታችን አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ እንደሚያደርግ ቃል እንገባለን::

6. የቅንጅትን እምነትና መርህ ተከትሎ ለፍትህ፣ ለሕግ የበላይነትና ለዲሞራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በአጠቃላይ ሀገራችንን ከድኅነትና ከኋላ ቀርነት ለማላቀቅ በቁርጠኝነት ከሚታገሉ የቅንጅት አመራር አባላት ጋር አቅማችን የፈቀደውን

መስዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጀን መሆናችንን እየገለጽን፣ በ 20/04/2000 ዓ.ም. የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የላዕላይ ም/ቤት ተሰብስቦ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች ሙሉ በሙሉ እንደግፋለን። ወደፊትም በላዕላይ ምክር ቤቱና የሥራ አስፈጻሚው በኩል የሚወጡ መመሪያዎችን ተከትለን የሚጠበቅብንን ማንኛውንም ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን እናረጋግጣለን።

ቅንጅት ሰላምና ፍቅርን መሰረት አድርጎ የዲሞክራሲ አሰራርን የሚያራምድ ድርጅት ነው!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!!

**በስዊዘርላንድ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት የካንቶን ተወካዮች ም/ቤት**
**ጥር** 8 **ቀን** 2000 **ዓ.ም.** (17.01.2008) **በርን**